➢ **እነሱንም በሦስት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡-**

**1ኛ የመጀመሪያዎቹና በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የነበሩት**

ዜገ ዜገ የሚል አስተምሕሮ ነበራቸው መምህራቸው እውር ዘኢየሱስ ይባላል ዜገ ማለት ደኸየ፣ አጣ፣ ተቸገረ ማለት ሲሆን ሰው በሆነ ጊዜ የባሕርይ ክብሩን ከዐይን ቅጽበት በሚቀድም ፍጥነት አጣ ለቀቀ ወዲያው በቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ ተቀበለ የባሕርይ ልጅ ሆነ ባዮች ናቸው፤ በእርግጥ አሁን አሁን እንደምናየው ዛሬም ይህ ክፉ ትምህርት ቀጥሏል ምክንያቱም ‹‹ቃል ሥጋን በመዋሐዱ ፈጣሪነቱን ሳይለቅ በሥጋ ርስት ፍጡር ደኀራዊ ሲሆን ጊዜ ሳይሻ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ ከአብ ቢወለድ በቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ አዋቂ ሐዲስ አምላክ ሆነ››(ወል.አብ ገጽ108) ብለው ስለጻፉ ነው።

እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሚጠትንና ውላጤን በአንድ ጊዜ ያሳይብናል፤ ቃል በመጀመሪያ ገዥ ነበር ሲዋሐድ ተገዥ ሆነ ሲቀባ እንደገና የባሕርይ አምላክ ሆነ እሚለውሚጠት ይባላል፤ ሥጋ ግን ቀድሞ ተገዥ ነበር ተለውጦ ገዥ ሆነ የሚለው ውላጤ ይባላል። ሚጠትና ውላጤ ደግሞ በምሥጢረ ሥጋዌ ውስጥ የሌሉ አባቶቻችን ያላስተማሩን እንዲያውም ያወገዟቸው ትምህርቶች መሆናቸውን በምሥጢረ ተዋሕዶ ላይ ስላየን እዚህ ላይ መድገም አያስፈልገንም።

**2ኛ. በአፄ ዮሐንስ ዘመን የነበሩት**

መምህራቸው አካለ ክርስቶስ ይባላል እነዚህ ደግሞ ከመጀመሪያው ዜገ የሚለውን ትምህርት ይነቅፉታል፤ ‹‹እስመ ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ የሚለውን የቄርሎስን ትምርት ከጠቀሱ በኋላ በተዋሕዶ ሁለትነት ጠፍቶ

